Montgomery County Public Schools
*የልጅ መጎሳቆልና ቸልታ ጉዳይ ዘገባ አቀራረብና ምርመራ አፈፃፀም መመርያዎች*
*(በተከለሰው የMCPS ደንብ JHC-RA ውስጥ የሚሰፍር)*

DRAFT: May 7, 2015

## I. ትርጉሞች

### A. ማጎሳቆል።

1. የአንድ ልጅ ወይም ደካማ/vulnerable አዋቂ ማንኛውም፣ ሊታይ ወይም ላይታይ የሚችል አካላዊ ጉዳት፣ ወይም የአእምሮ ጉዳት፣ ልጁን ወይም ደካማ አዋቂውን የመንከባከብ ጊዚያዊ ወይም ዘላቂ ጠባቂነት ወይም ሀላፊነት ባለው በማንኛውም ግለሰብ፣[1] የልጁ ወይም የደካማው አዋቂ ጤና ወይም ደህንነት በመጎዳት ላይ ወይም የመጎዳት ከፍተኛ አደጋ ላይ መሆኑን በሚያመለክት ሁኔታ መፈፀም።
2. ልጅን ወይም ደካማ/vulnerable አዋቂን የመንከባከብ ዘላቂ ወይም ጊዚያዊ ጠባቂነት ወይም ሀላፊነት ባለው በማንኛውም ግለሰብ ላይ የተፈፀመ ማንኛውም የፆታ ተግባር ወይም ተግባሮች (አካላዊ ጉዳቶች ይድረሱም አይድረሱም) ፣ የዘመድ የፆታ ግንኙነት፣ አስገዳጅ የፆታ ግንኙነት፣ ወይም በማንኛውም ደረጃ የፆታ ጥቃት፣ ግብረ ሰዶም ወይም ከተፈጥሮ ውጭ የፆታ ልምዶችን የሚጨምር ነገር ግን በነዚህ ያልተወሰነ። ፆታዊ አመፅ ወይም መጠቃት የሚያካትተው፣ ነገር ግን በዚህ ሳይወሰን፣ አላግባብ መጋለጥ፣ የፆታ ብልት/ተግባር የማየት ጉጉት፣ መሳም፣ በእጅ መዳሰስ፣ ፆታዊ መቀራረቦች፣ በማንኛውም ደረጃ የሚፈፀም የፆታ ወንጀል፣ አስገድዶ መድፈር፣ ግብረ ሰዶም፣ ሽርሙጥና፣ በሰው መነገድ፣ ወይም የግብረስጋ ግንኙነት ትርእይት፣ ፎቶግራፍ፣ ፊልም ማንሳት መፍቀድ፣ ማበረታታት፣ ወይም መሳተፍ፣ ወይም ልጅን ወይም ደካማ አዋቂን ከህግ ውጭ አድርጎ ማሳየት፣ ወይም አንድን ልጅ ወይም አንድን ደካማ አዋቂ ከለየለት/የተመዘገበ ፆታዊ አጥቂ አብሮ እንዲኖር ወይም በደምበኛነት አካባቢው እንዲገኝ መፍቀድ።

### B. **ልጅ**።
ማንኛው/ዋ የMCPS ተማሪ፣ እድሜው/ዋ የፈለገውን ይሁን፣ እና እድሜው/ዋ ከአስራስምንት አመት በታች የሆነ ማንኛው(ዋ)ም ግለሰብ። ምንም እንኳን የሜሪላንድ ህግ እድሜው/ዋ ከአስራስምንት አመት በላይ የሆነ/ች ልጅ መጎሳቆል ወይም ቸል ማለትን ውንጀልና ባያደርገውም፣ MCPS እንደዚህ አይነቱን ጠባይ ከዚህ በታች በሰፈረው ቅደም ተከተል/ሂደት ዘገባ እንዲደረግበት ይጠብቃል።

### C. **የካውንቲ ባለ-በርካታ ዲሲፕሊን ቡድን/County Multi-Disciplinary Team (MDT)**
የMontgomery County ወኪል ድርጅቶች ባለሙያዎች ቡድን እንደአስፈላጊነቱ የሚሰበሰብና ተገቢ ሆኖ ሲገኝም ምክርና የተቀናጀ ህክምና ፕላን የሚሰጥ። የካውንቲው MDT የሚያካትተው የMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ ማጎሳቆል ተጠሪ(ዎች) እና የሚከተሉት የMontgomery County ወኪል ድርጅቶች፡- (1) የMontgomery County ስቴት አቃቤ ፅ/ቤት፤ (2) በMontgomery County የፖሊስ መመርያ (MCPD) የልዩ ተጠቂዎች የምርመራ ክፍል፤ (3) በMontgomery County የጤናና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምርያ የልጅ ደህንነት አገልግሎቶች/Child Welfare Services፣ በነዚህ መመርያዎች በይፋ የልጅ መከላከያ አገልግሎቶች/Child Protective Services (CPS) ተብሎ የሚታወቅና የሚለይ፣ ወይም በMontgomery County የጤናና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምርያ የእርጅናና የስንክልና አገልግሎቶች መርጃና እርዳታ ጓድ/Aging and Disabilities Services Information and Assistance Unit፣ በነዚህ መመርያዎች በይፋ የአዋቂ መከላከያ አገልግሎቶች/Adult Protective Services (APS) ተብሎ የሚታወቅና የሚለይ፤ እና (4) የMontgomery County ትሪ ሀውስ የልጅ ግምገማ ማእከል/Tree House Child Assessment Center። በማጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት ጉዳዮች ተከሳሹ የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ ወይም ባለበጎ-ፈቃድ ሲሆን፣ የMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ/Child Abuse Contact መረጃዎችን ለማረጋገጥ እና ተገቢው እርምጃ መወሰዱን ለመወሰን፣ እንዲሁም የተወሰዱ ትምህርቶችን ለመገምገምና ለቀጣይ መሻሻል እድሎችን ሁኔታዎችን ለማብራራት፣ በMDT ስብሰባዎች ወይም ምክር ሊሳተፍ ይችላል። በተጨማሪም፣ አንድ የMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ ማጎሳቆል ተጠሪ በት/ቤታቸው ዘገባ ለቀረበበት ተማሪ እንክብካቤና የተቀናጁ አገልግሎቶች ለመስጠት ለማገዝ አላማ ብቻ የት/ቤት የልጅ መጎሳቆል አገናኝ መኮንን(ኖች)/School-Based Child Abuse Liaison(s)ን ሊጋብዝ ይችላል።

### D. **የMCPS የልጅ መጎሳቆል አስተባባሪ ቡድን**
ይህ ቡድን የልጅ መጎሳቆልና ቸልታ ዘገባ ለቀረበባቸው አጋጣሚዎች በMCPS ውስጥ የተቀነባበረ ምላሽ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል። ይህም የሚያካትተው የMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ(ዎች)/Child Abuse Contact(s) እንዲሁም የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ፅ/ቤት/Office of

---

[1]አንድን ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ ለመንከባከብ ወይም ለመቆጣጠር ዘላቂ ወይም ጊዚያዊ ጥበቃ ወይም ሀላፊነት ያለው ግለሰብ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ጉዲፈቻ ወላጅ፣ ቤተሰብ ወይም አብሮ የሚኖር፣ ጎረቤት፣ የMCPS ተቀጣሪ፣ ባለ በጎ-ፈቃድ ወይም ስራ ተቋራጭ፣ ወይም ሌላ ግለሰብን ያካትታል።

School Support and Improvement (OSSI)፣ የሰው ሀይልና ልማት ፅ/ቤት/Office of Human Resources and Development (OHRD)፣ የተማሪ አገልግሎት መምርያ/Department of Student Services (DSS)፣ የጠቅላይ ምክር ቤት ፅ/ቤት/Office of General Counsel (OGC)፣ የት/ቤት ደህንነትና ፀጥታ መምርያ/Department of School Safety and Security፣ የመገናኛ ፅ/ቤት/Office of Communications፣ የMCPS ታይትል IX አስተባባሪ/Title IX Coordinator፣ እና እንደ አግባቡ ሌሎች ፅ/ቤቶችና መምርያዎችን ነው።

E. **የቤተሰብ ወይም አብሮ የሚኖር አባል።** በተባለው መጎሳቆል ወይም ቸልታ ወቅት በልጅ ወይም በደካማ አዋቂ ቤት ውስጥ አብሮ የሚኖር ወይም በየጊዜው የሚገኝ ግለሰብ። በመኖርያ ቤት የሚኖር ማለት አንድን ግለሰብ የአንድ ልጅ፣ ወይም የደካ አዋቂ፣ ወይም የቤተሰብ ትርጉም ያዘለ አካል የሚያደርገው የመኖርያ ቤት ጉብኝት ወይም ቆይታ ማለት ነው።

F. **የአእምሮ ጉዳት።** የአንድ ልጅ ወይም የደካማ አዋቂ አንጎል ወይም የሳይኮሎጂ ችሎታ ለመስራት የመቻል የሚታይ፣ የሚለይ እና የተጨበጠ ጉዳት።

G. **የMCPS ሰራተኞች።** ተተኪ መምህራንን ጨምሮ፣ ሁለቱም መታወቂያ የተሰጣቸውና ያልተሰጣቸው/Both certificated and non-certificated በMCPS የተቀጠሩ ሰራተኞች።

H. **የMCPS ንብረት።** ማንኛውም ት/ቤት ወይም ሌላ መገልገያ፣ በMCPS ባለቤትነት ወይም አስተዳደር ስር የሚገኙ ቦታዎች፣ አውቶቡሶችና ሌሎች የMCPS ተሽከርካሪዎች፣ እና፣ የመስክ ጉዞዎችን ጨምሮ፣ ተማሪዎችን የሚያስተናግዱ በMCPS ስፖንሶር የሚደረጉ ማንኛቸውም የእንቅስቃሴ መገለያዎችንና ቦታዎች።

I. **የMCPS ስራ ተቋራጭ።** ለMCPS አገልግሎቶች የሚያቀርቡ የውጭ ስራ ተቋራጮችና ሌሎች ግለሰቦች፣ የስራ ተቋራጩ ቀጥተኛ ሰራተኞች፣ የበታች ስራ ተቋራጮች፣ እና/ወይም ከMCPS ጋር ባለው ውል መስረት ተፈላጊውን ስራ ለመፈፀም የስራ ተቋራጩ የሚጠቀምባቸው ነፃ የስራ ተቋራጮችን ጨምሮ። ይህ ደንብ በMCPS ስራ ተቋራጮች ላይ ተግባራዊ የሚሆነው ለMCPS አገልግሎቶች በሚያቀርቡበት ወቅትና ከMCPS ተማሪዎች ጋር፣ በMCPS ንብረት ላይ ወይም በMCPS ስፖንሶር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች መዳረሻ ወይም ግንኙነት ሲኖራቸው ነው።

J. **የMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ(ዎች)።** የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ/Deputy Superintendent for School Support and Improvement በት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ፅ/ቤት (OSSI) ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ(ዎች) ይወክላል፣ እሱም/እነሱም የMCPS የልጅ መጎሳቆል አስተባባሪ ቡድን ስብሰባ ለመጥራት እና ከካውንቲው በለ-ብዙ ዲሲፕሊን ቡድን/County Multi-Disciplinary Team ጋር ለመመካከር ተቀዳሚው የMCPS ስርአት-አቀፍ ተጠሪ(ዎች) ይሆናል/ይሆናሉ።

K. **የMCPS ባለ-በጎ ፈቃደኞች።** በጎ-ፈቃደኞች ወላጆች/አሳዳጊዎችና ሌሎች የቤተሰብ አባሎች፣ እንዲሁም በልጆች ትምህርት ፍላጎት ያላቸው የማህበረሰብ አባሎች፣ በMCPS ደንብ IRB-RA፣ *የት/ቤት በጎ-ፈቃደኞች* በመመስረት የMontgomery County ተማሪዎችን ለመደገፍ ግዜያቸውንና ሀይሎቻቸውን በነፃ የሚሰጡትን ያካትታል። ይህ ደንብ ከMCPS ተማሪዎች ጋር ቀጥታ መዳረሻ ወይም ግንኙነት ባላቸው የMCPS በጎ-ፈቃደኞች ላይ ተግባራዊ የሚሆነው፣ በጎ-ፈቃደኞቹ በMCPS ንብረት ላይ ሳሉ ወይም MCPS ስፖንሶር ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች በመሳተፍ ላይ እያሉ ነው።

L. **ቸልተኝነት።** አንድን ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ ያለ ጠባቂ መተው[2] ወይም ተገቢ እንክብካቤ ወይም ክትትል በመስጠት ብቁ ሳይሆኑ መገኘት፣ ወይም ተገቢ ያልሆነ እንክብካቤ ወይም ክትትል፣ ለአንድ ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ በአንድ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ የጉዲፈቻ ወላጅ፣ ዘመድ ወይም የቤተሰብ አባል፣ ጎረቤት፣ የMCPS ሰራተኛ፣ በጎ-ፈቃደኛ ወይም ስራ ተቋራጭ፣ ወይም የሚከተለውን በሚያመለክቱ የአንድ ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ ለመቆጣጠር

---

[2] በሜሪላንድ፣ አንድ እድሜው/ዋ ከስምንት አመት በታች የሆነ/ች ልጅ ያለ አጃቢ በቤት፣ በት/ቤት፣ ወይም በመኪና ውስጥ ብቻው(ዋ)ን መተው የለበ(ባ)ትም። እንድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ከስምንት አመት በታች የሆነ(ች)ውን ልጁን መተው ካስፈለገው፣ ወላጁ ወይም አሳዳጊው ቢያንስ አስራሶስት አመት እድሜ ያለው/ያላት አስተማማኝ ግለሰብ ልጅ(ጇ)ን ለመጠበቅ መቆየቱ(ቷ)ን ማረጋገጥ አለበ(ባ)ት። በሌላ በኩል፣ ወደ ት/ቤት በእግራቸው ለሚጓዙ ወጣት ተማሪዎችን በሚመለከት የሚቀርቡ ሀሳቦች በዚህ ድርጣብያ ይገኛሉ፡- http://www.montgomeryschoolsmd.org/parents/basics/transportation/

ዘላቂ ወይም ጊዚያዊ ጥበቃ ወይም ሀላፊነት ያለው ሌላ ሰው።

1. የልጁ/ጇቱ ወይም የደካማ አዋቂ ጤንነት ወይም ደህንነት መጎዳቱ ወይም ለጉዳት አስጊ ሁኔታ ላይ መገኘቱ፣ ወይም
2. የአእምሮ ጉዳት ለልጅ ወይም ለደካማ አዋቂ ወይም ለጉዳት አስጊ ሁኔታ።

M. **በት/ቤት የሚገኙ የልጅ መጎሳቆል አገናኝ መኮንን/ኖች።** እያንዳንዱ/ዷ ርእሰመምህር አንድን የት/ቤት አማካሪ ወይም ሌላ የሰራተኞች አባል በት/ቤቱ የልጅ መጎሳቆል አገናኝ መኮንን እንዲ(ድት)ሆን ይሰይማል/ትሰይማለች። በት/ቤት የሚገኘው/የምትገኘው የልጅ መጎሳቆል አገናኝ መኮንን በት/ቤት ለሚገኙ ሰራተኞች መጎሳቆልና ቸልተኛነትን በመለየት፣ በዘገባ፣ እና በመከላከል ሞያዊ ስልጠና በመስጠት ያግዛል/ታግዛለች። መጎሳቆል ወይም ቸልተኛነት ደርሷል የሚል ዘገባ ከቀረበ በኋላ፣ በት/ቤት የሚገኘው የልጅ መጎሳቆል አገናኝ መኮንን የት/ቤቱ ርእሰመምህሩ/ሯ ለስሞታው አፀፋ ሲወስድ/ስትወስድ መደገፍ እና ለካውንቲው MDT ተባባሪ ወኪል ድርጅቶች መገናኛ በመሆን እና ተጠቂ ለተባለ(ች)ው ተማሪ ድጋፍ አስተባባሪ ሆኖ በማገልገል ያግዛል/ታግዛለች። በተጨማሪ፣ በት/ቤት የሚገኙ የልጅ መጎሳቆል አገናኝ መኮንኖች በት/ቤታቸው ዘገባ ለቀረበበት ተማሪ እንክብካቤና የተቀነባበረ አገልግሎቶች ለመስጠት ለማገዝ አላማ ብቻ በካውንቲ MDT ስብሰባ ወይም ምክክር እንዲቀላቀሉ በMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ ሊጋበዙ ይችላሉ። በት/ቤት የሚገኙ የልጅ መጎሳቆል አገናኝ መኮንኖች መጎሳቆልንና ቸልተኝነትን በመለየት፣ በማመልከት እና በመከላከል አላማ ያለው ሙያዊ ስልጠና ይቀበላሉ።

N. **ግብረመልስ/Retaliation።** አንድን ግለሰብ የማስፈራራት ወይም አለዝያ የመቅጣት ተግባር ወይም ሂደት፡- (1) ህግ፣ መመርያ፣ ወይም ደንብ ጣሰ/ች ብሎ/ላ በማመልከቱ/ቷ፤ ወይም (2) ተፈፀመ በተባለ ጥሰት ምርምራ በመሳተፉ/ፏ።

O. **ደካማ/vulnerable አዋቂ።** መጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በሚያመለክት ግለሰብ የእለት ፍላጎቱ(ቷ)ን ለመንከባከብ አካላዊ ወይም የአእምሮ ችሎታ የለውም/የላትም ተብሎ በግለሰብ ዘገባ የቀረበ(ባ)ት የአስራስምንት አመት ወይም ከዚያ በላይ እድሜ ያለው/ያላት ግለሰብ።

## II. <u>ለMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች ዘገባ የማቅረብ ሀላፊነት</u>

A. **ዘገባ የማቅረብ ሀላፊነት መጠን።** ሁሉም የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች በግለሰብ ደርጃና በቀጥታ ማንኛውንም የተጠረጠረ የልጅ ወይም የደካማ አዋቂ መጎሳቆል ወይም ቸልታ ማመልከት/ዘገባ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡

1. ተጠቂ የሚባለው/የምትባለው በግለሰብ ደረጃ በአመልካቹ/ቿ ይታወቅ/ትታወቅ እንደሆነና እንዳልሆነ።

2. ጥቃቱ ባለፈው ጊዜ መድረሱ ለማመን እስከተቻለ ድረስ፣ ምንም እንኳን ሁኔታው በተጋለጠ ወቅት ተጠቂው/ዋ አዋቂ ቢሆንም/ብትሆንም።

3. ልጁ/ልጂቱ ወይም ደካማው/ዋ አዋቂ የትም ይኑር/ትኑር እናም የተጠረጠረው መጎሳቆል ወይም ቸልታ ተፈፅመበት የተባለው የትም ቦታ ይሁን።

B. **የቃል ማመልከቻ/ዘገባ።** የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች ስለተጠረጠረ መጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በአፋጣኝ የቃል ዘገባ ማቅረብ አለባቸው።

1. **የCPS/APS ማስታወቂያ** እያንዳንዱ መጎሳቆሉን ወይም ቸልታውን የጠረጠረ የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ የቃል ዘገባ/ማስታወቂያ መደረጉን ማረጋገጥ የግል ሃላፊነት አለበት።

   a. የልጅ መጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት የቃል ዘገባዎች፣ የ24 ሰአት የቴሌፎን አገልግሎት (240-777-4417) ለሚንከባከበው፣ ለCPS ወድያውኑ መደረግ አለባቸው።

   b. የደካማ አዋቂ ማጎሳቆል ወይም ቸልታ የቃል ዘገባዎች መደረግ ያለባቸው ለMontgomery County የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምርያ ለእርጅናና ስንክልና አገልግሎቶች መረጃና እርዳታ ጓድ/ Aging and Disabilities Services Information and Assistance Unit in the Montgomery County Department of Health and Human Services (240-777-3333) ነው።

   c. አንድ/አንዲት ገለሰብ ማጎሳቆል ወይም ቸልታ ስለማስታወቅ ጥርጣሬ ካለው/ካላት፣ ሁኔታውን ለCPS

(ወይም ለAPS ለደካማ አዋቂዎች) የማስመዝገብ አማራጭ መውሰድ ይገባዋ(ታ)ል።

d. ስለተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ ከመደረጉ በፊት፣ የተጠረጠረው ጥቃት ወይም ቸልታ ጉዳይ ዋጋ እንዳለው ለመወሰን ምርምራ ማካሄድ የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ሚና አይደለም።

e. አንድ/አንዲት ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ ስለተጠረጠረው ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት የሚመለከት መረጃ ለMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ከሰጠ/ች፣ ያ ግለሰብ ስለክውነቱና ጉዳቶች አጭር መግለጫ፣ የት እንደተደረጉ፣ እና እጥቂ ስለተባለው ስም ወይም አጭር መግለጫ ለማግኘት የተወሰኑ ተከታይ ጥያቄዎች ሊያቀርብ ይችላል። ዘገባ ከመደረጉ በፊት፣ የሆነ ሆኖ፣ የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች ከተደጋገመ፣ ዝርዝር ቃለ-መጠይቅ ሊፈጠር የሚችል አእምሮ የሚያዛባ ሁኔታ ለመከላከል ከማንኛውም ተጠቂ ወይም ምስክር ከተባለ/ች ጥያቄና መልስ ወይም የፅሁፍ መግለጫ መጠየቅ የለባቸውም።

f. ዘገባ ከመደረጉ በፊት፣ የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች አጥቂ የተባለ(ች)ውን የቃለ መጠይቅ ማድረግ ወይም ተደረገ ስለተባለው ከሱ/ሷ ጋር መወያየት አይገባቸውም።

g. መጎሳቆል ወይም ቸልታ ስለመኖሩ ለመጠርጠር በቂ ምክንያት መኖሩን ለመወሰን የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች የመጎሳቆልን ወይም የቸልታን ክስ ተማሪዎች ስህተት መሆኑን እንዲክዱ ወይም እንዲያጋንኑ መገፋፋት የለባቸውም።

2. **የርእሰመምህር/የበላይ ተቆጣጣሪ/Supervisor ማስታወቂያ።** ለCPS (ወይም ለAPS ለደካማ አዋቂዎች) ዘገባ ከተደረገ በኋላ፣ የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ፣ ዘጋቢው ግለሰብ ት/ቤት የሚገኝ ከሆነ፣ ለርእሰመምህሩ/ሯ ወድያውኑ ማስታወቅ አለበ(ባ)ት። ዘጋቢው ግለሰብ ት/ቤት የማይ(ት)ገኝ ከሆነ፣ እሱ ወይም እሷ ቀጥታ የበላይ ተቆጣጣሪው(ዋ)ን እንዲሁም የልጁ/ጇቱ ወይም የደካማው/ዋ አዋቂ የሚከታተለውን/የምትከታተለውን የት/ቤት ርእሰመምህሩ(ሯ)ን እንደአግባቡ ያሳውቃል/ታሳውቃለች። CPS ወይም APS አመልካቹ(ቿ)ን/ዘጋቢው(ዋ)ን ምርመራውን እየተወ(ች)ው ወይም እያካሄደ(ች)ው መሆኑን ቢነግርም/ብትነግርም ማስታወቂያው የግድ መሰጠት አለበት።

a. ማስታወቂያው እንደደረሰ፣ ርእሰመምህሩ/ሯ ወይም የበላይ ተቆጣጣሪው/ዋ ከዚህ በታች በክፍል 3 በተቀመጠው መሰረት ተከታይ ቅደም-ተከተሎችን ይጀምራል፣ እናም የMCPDን የልዩ ተጠቂዎች ምርምራ ክፍል/Special Victims Investigations Divisionን ታች በሚገኘው ክፍል 2(B)(4)(c) በተቀመጡት ሁኔታዎች ይገናኛል/ትገናኛለች።

b. ለCPS (ወይም APS ለዳካማ አዋቂዎች) አንዴ ዘገባ ከቀረበ በኋላ፣ ርእሰመምህሩ(ሯ)ም ሆነ/ች ማንኛውም ሌሎች የMCPS ሰራተኞች፣ ታች በክፍል 3 እንደተቀመጠው በስተቀር፣ ተጨማሪ የውስጥ ምርመራ ማካሄድ የለባቸውም።

c. ርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ቀጥታ ተቆጣጣሪው እላይ በክፍል 2(B)(1) በተገለፀው መሰረት የቃል ዘገባ መደረጉን እና ታች በክፍል 2(C) እንደተገለፀው የፅሁፍ ዘገባ መደረጉን ማረጋገጥ አለባቸው።

d. ይህ ደንብ የርእሰመምህሩ/ሯ ወይም የተቆጣጣሪ ማስታወቂያ ቢያስፈልገውም፣ የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች የዘገባ ግዴታዎቻቸውን አያሟላም። እላይ እንደተገለፀው፣ ለCPS (ወይም APS ለዳካማ አዋቂዎች) በግለሰብ ደረጃና በቀጥታ ማመልከትም በተጨማሪ ይፈለግባቸዋል።

e. የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ለት/ቤቱ/ቷ ወይም ለቀጥታ ተቆጣጣሪ/አለቃ ስለ ማስታወቅ ቅሬታ በሚኖረው/ራት ሁኔታዎች፣ በነዚህ ፈንታ ዘገባ አቅራቢው/ዋ ለMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ ማሳወቅ ይችላል/ትችላለች።

f. የቃል ዘገባ የሚያቀርበው/የምታቀርበው የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ዘገባውን በሚመለከት ወይም ከሱ ጋር ግንኙነት ባለው የካውንቲ MDT ውስጥ ከሚሳተፍ CPS፣ MCPD፣ ወይም ሌላ ወኪል ድርጅት ጋር የተካሄደ ተጨማሪ ምክክር ወይም የሚገኝ መረጃ እንደአግባቡ ለርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ለቀጥታ አለቃው/ዋ ወድያውኑ ይሰጣል/ትሰጣለች።

3. **የMCPD ማስታወቂያ።** የዘገባዎችን ክትትል ለማቃለልና ለማመቻቸት፣ MCPS እና የካውንቲው MDT አባሎች CPS፣ ወይም APS ዳካማ አዋቂዎችን በሚመለከት፣ ለMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች ተቀዳሚ የዘገባ ወኪሎች እንዲሆኑ ተስማምተዋል። በተጨማሪ፣ የካውንቲው MDT ወሳኝ

አባል እንደመሆኑ፣ የMontgomery County የፖሊስ መመርያ (MCPD) የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል በየወቅቱ ምክር ይጠየቃል፣ እናም የተጠረጠሩ የመጎሳቆል ወይም የቸልታ ክውነቶች ሲኖሩ፣ ከዚህ በታች እንደሰፈረው፣ ወድያውኑ እንዲያውቀው ይደረጋል፡-

a. CPS (ወይም APS ለዳካማ አዋቂዎች) ወደ ወንጀለኛነት ደረጃ የሚያደርስ የመጎሳቆል ወይም የቸልታ ሁኔታ የሚያካትት ዘገባ ሲደርሰው/ሳት፣ የMCPS ግንዛቤ CPS (ወይም APS ለዳካማ አዋቂዎች) ወድያውኑ የMCPDን የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል እንደሚገናኝ ነው።

b. ማንኛውም በቁጥጥራቸው ስር የሚገኝ የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ለCPS (ወይም APS ለዳካማ አዋቂዎች) በቀጥታ ዘገባ ማቅረቡን ከማረጋገጥ ባሻገር፣ ርእሰመምህራኖች እና ተቆጣጣሪዎች፣ በክፍል 1(A)(2) እላይ እንደተገለፀው፣ የፆታ አመፅ ክስ ወይም አዋቂ ተጠቂን ያካተተ የፆታ አመፅ የማጎሳቆል ጥርጣሬ ከደረሳቸው፣ የMCPDን የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል ወድያውኑ ያሳውቃሉ።

c. ለሌሎች የተጠረጠሩ የመጎሳቆል ወይም የቸልታ ድርጊቶች አጸፋ መልስ ሲሰጡ፣ የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች የMCPDን የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከላይ እንደተገለፀው ለCPS (ወይም APS ለዳካማ አዋቂዎች) በግለሰብ ደረጃና በቀጥታ አሁንም የመመዘገብ ግዴታቸውን ማሟላት አለባቸው።

C. **የፅሁፍ ዘገባ** የማጎሳቆል ወይም የቸልተኛነት የቃል ዘገባ የሚያቀርብ/የምታቀርብ ግለሰብ ለCPS (ወይም APS ለዳካማ አዋቂዎች) በMCPS ፎርም 335-44፡- *የተጠረጠረ ማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኛነት ዘገባ* የፅሁፍ ዘገባ ማቅረብ አለበ(ባ)ት።

1. የፅሁፍ ዘገባው ለCPS (ወይም APS ለዳካማ አዋቂዎች) የግድ መቅረብ ያለበት ሊደርስ የሚችል ማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት መኖሩ የሚገልፅ መልእክት እንደደረሰ በ48 ሰአቶች ውስጥ ነው። ምንም እንኳን CPS፣ APS፣ እና/ወይም MCPD ምርመራውን መቀፀል የተወውና ፋይሉን እየዘጋው መሆኑን ለዘገባ አቅራቢው ያስታወቀ ቢሆንም፣ የፅሁፍ ዘገባው የግድ መደረግ አለበት።

2. ርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ቀጥተኛ ተቆጣጣሪ/አለቃ፣ በMCPS ፎርም 335-44 እንደተመለከተው፣ የዘገባውን ቅጂ፣ ቅጅዎችን በሚስጢራዊ ማህደር ለሚይዘው፣ ለMCPS የተማሪ አገልግሎት መምርያ ማሰራጨት አለበት። የማጎሳቆል ጉዳዮች ብቻ በሚመለከት፣ ርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ቀጥተኛ ተቆጣጣሪ/አለቃ የዘገባውን ቅጂዎች ለMCPD እና ለMontgomery County ስቴት አቃቤ ፅ/ቤት ማሰራጨት አለበት። ሁሉም ዘገባዎችና ቅጂዎች በመደበኛ ኤንቬሎፕ፣ ታሽገው፣ አድራሻ ተፅፎባቸው፣ እና ምስጢር የሚል ምልክት ተደርጎባቸው ይላካሉ። ኤንቬሎፑ በተለመደው የቢሮ-ለቢሮ ፖስታ መሸፈን አለባቸው።

3. ርእሰመምህሮች እና ተቆጣጣሪዎች የዘገባዎቹን ቅጅዎች መያዝ የለባቸውም፣ ነገር ግን የሁሉንም የተዘገቡ ጉዳዮች ምስጢራዊ ዝርዝር የሚከተሉትን ብቻ የሚያካትቱ ይይዛሉ፡- (a) የልጁ/ጇቱ ወይም የደካማ አዋቂ ስም፤ (b) አጥቂ የተባለ(ች)ው ስም፣ ከታወቀ፤ (c) የቃል ዘገባው ቀንና ሰአት፤ (d) ዘገባ የቀረበለት ሰራተኛ አባል ወይም ወኪል ድርጅት ስም፤ (e) ፎርሙ በፖስታ የተላከበት እለት።

## III. <u>ክሶቹ ከተዘገቡ በኋላ የክትትል ሀላፊነቶች</u>

### A. ምርመራዎች

1. MCPS ሰራተኞቹ፣ ስራ ተቋራጮቹ፣ እና በጎ-ፈቃደኞቹ በተጠረጠረ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት ምርመራዎች ከካውንቲው MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶችና ሌሎች ወኪል ድርጅቶች ጋር ሙሉ በሙሉ እንዲተባበሩ ይጠብቃል። የነዚያን ወኪል ድርጅቶች ምርመራዎች በሚመለከት መረጃ የመጋራት የጊዜ ቅደም ተከተሎች በMCPS እና በካውንቲው MDT አባሎች መካከል በተደረገው ስምምነት/Memorandum of Understanding ተቀምጠዋል። የካውንቲው MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ምርመራዎቻቸው በወቅቱ መከናወናቸውንና በመማርያ ክፍልና በት/ቤት ማህበረሰብ ረብሻ ለማሳነስ ከMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ/ዎች እና ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር ለመመካከር ተስማምተዋል።

2. የአንድ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ምርመራ ወቅት፣ CPS፣ APS፣ እና/ወይም MCPD አንድን ተማሪ በMCPS ንብረት ላይ/ውስጥ በትምህርት ሰአቶች መጠየቅ ይችላሉ። የት/ቤት ሀላፊ በጥያቄው ወቅት መገኘት እንዳለበት ርእሰመምህሩ/ሯ ይወስናል/ትወስናለች። ይህ ሲወሰን ርእሰመምህሩ/ሯ እንደአግባቡ ከካውንቲው MDT ወኪል ድርጅቶች ተወካይ ሰራተኞች እና ከMCPD ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ

ጋር መወያየት ይችላል/ትችላለች የወላጆች/አሳዳጊዎች ማሳወቅ ሁኔታ በክፍል 3.D.፣ ታች፣ ተገልፆአል።

3. የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎፈቃደኞች CPSን፣ APSን፣ እና/ወይም MCPDን የማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ምርመራ የሚያደናቅፍ ማንኛውንም ተግባር፣ ለምሳሌ አጥቂ ለተባለ(ች)ው ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ ተደርጎበታል ብሎ መንገር፣ መፈፀም የለባቸውም። ተጠቃ/ች የተባለ(ች)ውን ለማስተናገድ ወይም ለመጠበቅ በMCPS በኩል ተቀዳሚ መጠይቅ ወይም እርምጃ መወሰድ እስካለበት ድረስ ወይም ስለሌሎች ልጆች ወይም ደካማ አዋቂዎች የተሻለ ጥቅም ሲባል፣ ያ መጠይቅ ወይም እርምጃ ከካውንቲው MDT ጋር በመመካከር መከናወን ይኖርበታል።

## B. በMCPS ንብረት ወይም የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎፈቃደኞችን የሚያካትት የማጎሳቆልና የቸልታ ክሶችን የማስተናገድ ተጨማሪ ቅደም ተከተሎች

1. **ክትትል በርእሰመምህር ወይም ቀጥተኛ ተቆጣጣሪ።** አንድ ርእሰመምህር ወይም ቀጥተኛ ተቆጣጣሪ ከCPS (ወይም APS ለዳካማ አዋቂዎች) በMCPS ንብረት የመጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት ክስ ወይም በMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎፈቃደኛ የመጎሳቆልን ወይም የቸልተኝነትን ክስ የሚያካትት የቃል ዘገባ ማስታወቂያ ከተቀበለ/ች በኋላ ወድያውኑ የሚከተሉትን ተጨማሪ እርምጃዎች ይወስዳል/ትወስዳለች።

    a. በክፍል 3 እላይ እንደተቀመጠው፣ ለCPS (ወይም APS ለዳካማ አዋቂዎች) የቃል ዘገባ መድረሱን፣ እና ከዚያ በኃላ በ48 ሰአቶች ውስጥ የፅሁፍ ዘገባ ገቢ መሆኑን ማረጋገጥ።

    b. ለMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርምራዎች ክፍል፣ በክፍል 3 እላይ በተቀመጠው መሰረት፣ ፆታዊ አመፅ የሚያካትቱ የተጠረጠሩ ሁኔታዎችን ማሳወቅ

    c. ከMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ ማጎሳቆል ተጠሪ ጋር ተገናኝቶ ማማከር።

    d. ተጠቂ የተባለውንና የሌሎች ተማሪዎችን ደህንነት ለመጠበቅ የስራ አፈፃፀም ፕላን ማዳበር። በተቻለ መጠን፣ ፕላኑ መዘጋጀት ያለበት ከMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ ማጎሳቆል ተጠሪ ጋር በመተባበር ነው፣ እናም የልጆችንና የደካማ አዋቂዎችን ይበልጥ የተሻለውን ጥቅሞች ለመጠበቅ እስካልሆነ በስተቀር የተጠረጠረው ምጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ መደረጉን አጥቂ ለተባለው ከመንገር መቆጠብ።

    e. በክፍል 3(D) ታች የተቀመጡትን እርምጃዎች በመከተል፣ ስለ ተማሪ ተጠቂዎች ወላጆችን/አሳዳጊዎችን በተቀላጠፈ ሁኔት ለማስታወቅ ፕላን ለማዘጋጀት፣ እንዲሁም በክፍል 3(E) ታች የተቀመጡትን እርምጃዎች በመከተል፣ በማህበረሰቡ የሚገኙ ሌሎችን ማሳወቅ አስፈላጊ ከሆነ ይህንኑ የሚያስችል ፕላን ለማዘጋጀት ከMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ ማጎሳቆል ተጠሪ ጋር መተባበር።

2. **ክትትል በMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ ማጎሳቆል ተጠሪ።** ተፈፀመ ስለተባለው ማጎሳቆል ወይም ቸልተኛነት የዘገባ ማስታወቂያ እንደደረሰ፣ የMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ ማጎሳቆል ተጠሪ የሚያደርገው፡-

    a. ለሁኔታው ምላሽ ሲሰጥ ለርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ለቀጥተኛ ተቆጣጣሪ ተገቢውን ድጋፍ ለመስጠት፣ OSSIን ጨምሮ፣ ከMCPS የልጅ ማጎሳቆል አስተባባሪ ቡድን አግባብ ካላቸው አባሎች ጋር መመካከር።

    b. ከCPS፣ ከMCPD፣ እና ከሌሎች የካውንቲ MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ጋር እንደአስፈላጊነቱ ግንኙነት መመስረቱን ማረጋገጥ። የካውንቲው MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ለMCPS የምክር ጥያቄዎች ወድያውኑ መልስ ለመስጠት ተስማምተዋል፣ በተለይም እነዚህን የስራ ፕላኖች ዝግጅት በሚመለከት፡- (1) ስለ ተማሪ ተጠቂዎች ወላጆችን/አሳዳጊዎችን አቀላጥፎ ማሳወቅ፤ እና (2) አጥቂ የተባለው በተጠቂ በተባለውና በሌሎች ተማሪዎች ደህንነት የቅርብ አደጋ ሆኖ እንዳይገኝ።

    c. አጥቂ ነው የተባለው የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ከሆነ OHRDን መገናኘት።

    d. ከርእሰመምህሩ(ሯ) እና ት/ቤት የሚገኘውን የልጅ ማጎሳቆል አገናኝ መኮንን የመርዳትና ቀጣይ ምክክር ማስተባበር።

3. **ክትትል በOHRD** አጥቂ ነው የተባለው የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ከሆነ፣ OHRD የሚያደርገው፡-

    a. የጉዳይ ማህደር መክፈት።

b. አጥቂ የተባለውን የሚመለከት ሌላ አግባብ ያለው መረጃ መኖሩን ለመወሰን የሰራተኛ ማህደሮችን መገምገም።

c. ምርመራው በእንጥልጥል ላይ እያለ፣ አጥቂ የተባለውን በአስተዳደራው ፈቃድ እንዲቆይ አልያም ተማሪዎች ጋር እንዳይደርስ ለመድረግ፣ ከርእሰመምህሩ/ሯ/ተቆጣጣሪው/ዋ፣ ከMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ ማጎሳቆል ተጠሪ፣ ከMCPS የልጅ ማጎሳቆል አስተባባሪ ቡድን፣ እና ከካውንቲው የMDT ተባባሪ ወኪል ድርጅቶች ጋር በመተባበር ፕላን ማዘጋጀት።

1) OHRD አንድን የMCPS ሰራተኛ አስተዳደራዊ ፈቃድ ላይ ያቆየዋል፣ ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ አስፈላጊ የሚያደርግ ትርጉም ያዘለ፣ የሚያሳምን መረጃ እስካልተገኘ ድረስ።
2) አጥቂ የተባለው ስራ ተቋራጭ ከሆነ፣ ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ አስፈላጊ የሚያደርግ ትርጉም ያዘለ፣ የሚያሳምን መረጃ እስካልተገኘ ድረስ፣ አቅራቢውን ለማስታወቅና ምርመራው እስኪፈፀም በማጎሳቆል ወይም ቸልተኛነት በተጠረጠረው ግለሰብ የሚቀርቡትን አገልግሎቶች ለማቋረጥ OHRD ከሌላ በOffice of the Chief Operating Officer/ዋና የስራ መኮንን ፅ/ቤት (OCOO) ከሚገኝ ሰራተኛ ጋር ይሰራል።
3) አጥቂ የተባለው በጎ-ፈቃደኛ ከሆነ፣ ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ አስፈላጊ የሚያደርግ ትርጉም ያዘለ፣ የሚያሳምን መረጃ እስካልተገኘ ድረስ፣ ምርመራው እስኪፈፀም ድረስ፣ ግለሰቡ በMCPS ንብረት ወይም MCPS ስፖንሰር በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች በበጎፈቃደኝነት እንዳይደርስ ለማገድ OHRD ከOSSI እና OCOO ጋር አብሮ ይሰራል።
4) ይህ ፕላን ተግባራዊ ሲደረግ፣ የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ከአስተዳደራዊ ፈቃድ፣ የአገልግሎቶች መቋረጥ፣ ወይም ከበጎ-ፈቃድ ልዩ መብቶች መታገድ ጋር በቀጥታ የተያያዙ ዝርዝሮች ብቻ እንዲነገረው/እንዲነገራት ለማረጋገጥ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። የMCPS ሰራተኞች፣ በውጭ ወኪል ድርጅቶች በመካሄድ ላይ የሚገኙ የእንጥልጥል ምርመራዎች ብቃት ከማደናቀፍ ለመቆጠብ፣ የካውንቲውን MDT በቅድሚያ ሳያማክሩ ክሶቹን አጥቂ ከተባለው ጋር መወያየት የለባቸውም።

d. **የMCPS ተከታይ ምርመራ።** የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ በማጎሳቆል ወይም በቸልተኛነት በተጠረጠረ ቀጥር፣ OHRD ከሁሉም የሚመለከታቸው የMCPS መመርያዎችና ደንቦች በሚስማማ መንገድ የውስጥ ምርመራ ያካሂዳል፣ እናም ተገቢ የዲሲፕሊን እርምጃ ሀሳብ ያቀርባል። ምንም እንኳን CPS እና MCPD ጉዳዩን አጣርተው ብቃት የለውም ቢሉ ወይም እርምጃ ሳይወስዱ ቢዘጉት እና/ወይም የስቴቱ አቃቤ ህግ እንደነዚህ አይነቶቹ የMCPS መመርያዎች፣ ደንቦች፣ ውሎች እና/ወይም የሰራተኛ ስነምግባር ደንብ/Employee Code of Conductን ጨምሮ ሌላ አመራርን ጥሰቶች ሊያካትቱ ስለሚችሉ የወንጀለኛ ክስ አልመሰርትም ቢልም፣ OHRD የውስጥ ምርመራ ያካሂዳል።

1) የMCPS የውስጥ ምርመራዎች ሊካሄዱ የሚችሉት ከካውንቲው MDT ተባባሪ ወኪል ድርጅቶች ከተመካከሩ በኋላ እና በMCPS እና በካውንቲው MDT ተባባሪ ወኪል ድርጅቶች መካከል በተደረገው የጋራ ስምምነት/Memorandum of Understanding መሰረት ብቻ ነው። ይህን የመሳሰለው ምርመራ መካሄድ ያለበት በCPS፣ በMCPD፣ ወይም በሌሎች ወኪል ድርጅቶች የሚካሄድ ምርመራ ወስጥ ጣልቃ በማይገባ ወይም በማያጫናግፍ መንገድ ነው።
2) በተቻለ መጠን፣ የMCPS ምርመራ፣ በተብራራው የሜሪላንድ ህግ፣ የሰው አገልግሎቶች አንቀፅ፣ ክፍል 1-202 መሰረት ተጠቂ የተባሉትንና የምስክሮች የቃለ-መጠይቅ ድግግሞሽ በቅድሚያ ለመቀነስ፣ በፖሊስ ዘገባዎች፣ መግለጫዎች፣ እና በMDT ተባባሪ ድርጅቶች በተገኙ መረጃዎች መገልገል ያስፈልጋል።

3) የMCPS ምርመራ ተቀዳሚ አላማ በMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ የስነምግባር ጉድለት ማስረጃ እንዳለ ለማጣራት ነው። በተጨማሪ፣ ምርመራው ጉዳዩ በህግ እንደሚፈለገውና በMCPS መመርያና ደንቦች መሰረት ተዘግቦ መሆኑን፣ እና ሞያዊ ብልፅግና ወይም የሂደት መሻሻሎች ያስፈልጉ እንደሆነ ማጣራት አለባቸው።

4) ምርመራዎቹ የMCPS ሰራተኞችን ህጋዊ መብቶችን በሚመለከት የMCPSን መመርያዎችን እና ደንቦችን ማሟላት አለባቸው፣ ሰራተኛውም የምርመራው ውጤት እንዲነገረው ያስፈልጋል።

5) የምርመራው ውጤት በሚስጥራዊ የOHRD ማህደር ግለሰቡ ለMCPS አገልግሎት መስጠት እስከቀጠለበት ድረስ ወይም ቢያንስ ለአምስት አመቶች ከዚያ በኋላ ይያዛል። ከዚያም ማህደሮቹ

በቋሚ መጋዘን ይቀመጣሉ።

6) የOHRD ሚስጢራዊ ማህደሮች ተደርገዋል ስለሚባሉ የሰራተኛ ስነምግባር ህግ/Employee Code of Conduct ጥሰቶች፣ እንዲሁም ሌሎች በተማሪዎችና በMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች መካከል የአላግባብነት እምቅነት ያላቸው በተናጥል ለማጎሳቆል ወይም ለቸልተኝነት ለመጠርጠር ብቁ ያልሆኑ ነገር ግን ተጨማሪ መረጃ ከተከሰተ፣ የዚህ አይነቱ ጠባይ ከተደገመ፣ ወይም አንድ ቅርፀት ከተለየ፣ ተጨማሪ ምርመራ የሚገባ ሆኖ ከታየ ይህንን አስመልክተው በርእሰመምህራን/ተቆጣጣሪዎች የተዘገቡ መረጃዎችን ይከታተላሉ።

## C. የተማሪ ድጋፍ አገልግሎቶች

1. አንድ ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ በማጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት በተባለ ሁኔታ ከተያያዘ/ች አስቸኳይ ህክምና ወይም የአእምሮ ጤና ህክምና ካስፈለገው/ጋት፣ ርእሰመምህሩ/ሯ ወይም የርእሰመምህሩ/ሯ ወኪል በአዋቂ ቁጥጥር ስር ወደ ሆስፒታል ወድያውኑ እንዲላክ/እንድትላክ ያደርጋል/ታደርጋለች። ከዚያ በተከታታይ ወይም ወድያውኑ የCPS (ወይም APS ለዳካማ አዋቂዎች) ተወካይ እንዲያውቀው ይደረጋል። በሌሎች አስቸኳይ ባልሆኑ ጉዳዮች በሞላ፣ MCPS የልጅ ወይም የደካማ አዋቂ የአካልና የአእምሮ ጤንነት ህክምናን በሚመለከት CPSን፣ APSን፣ ወይም MCPDን ያማክራል።

2. በት/ቤት የሚገኘው የልጅ ማጎሳቆል አገናኝ መኮንን የማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ክሶች ለማመልከት ወይም ለማረጋገጥ ለሚቀርቡ ተማሪዎች ድጋፍና ምክር ለመስጠት የአመራር አማካሪዎች፣ የት/ቤት ሳይኮሎጂስቶች፣ ፒውፒል ፔርሶኔል ሰራተኞች፣ ነርሶች፣ እና ሌሎች አግባብ ያላቸው የት/ቤት ስርአት ሰራተኞች መገኘታቸውን ያረጋግጣል።

3. የማጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት ተጠቂ ለተባለው፣ እንዲሁም ማጎሳቆልና ቸልተኝነት ለሚያመለክቱ ተማሪዎች አገልግሎቶች ለማስተባበር፣ መረጃዎች ለመጋራት ወይም ለማግኘት፣ ወይም በቅሬታዎች ለመወያየት፣ የMCPSን ሰራተኞችና ተማሪዎች ምስጢራዊነት የሚጠብቁ ህጎች እስከፈቀዱ ድረስ፣ የMCPD ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ ከካውንቲ MDT ተባባሪ ወኪል ድርጅቶች ጋር መወያየት ይችላል። የMCPS ሰራተኞች በMCPS እና በሌሎች የMDT ወኪል ድርጅቶች መካከል በተቋቋሙ ቅደም-ተከተል ሂደቶች መሰረት በMDT ስብሰባዎች ወይም ምክክሮች መሳተፍ ይችላሉ።

4. የMCPS ርእሰመምህር የማጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት ምርመራ ተጠያቂ ምርመራው ከተጀመረ በሶስት ወሮች ውስጥ ከቤቱ/ቷ አካባቢ ት/ቤት ረሱ/ሷን ማግለሉ/ሏ ወይም እንዲወጣ/እንድትወጣ መደርጉ ሲከሰትለ(ላ)ት፣ ርእሰመምህሩ/ሯ የMCPD ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ ማሳወቅ አለባት፣ እሱ(ሷ)ም በተራው/ዋ፣ እንደአግባቡ ከካውንቲ MDT ተባባሪ ወኪል ድርጅቶች ጋር ይመካከራል/ትመካከራለች።

## D. የተጠቁ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎችን ማስታወቅ

1. ርእሰመምህራን፣ ከMCPD ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ ጋር በመተባበር፣ እንደዚህ አይነቱ ማስታወቂያ ለልጁ ደህንነት ስጋት የሚፈጥር እስካልሆነ ድረስ (ለምሳሌ አንድ የወላጅ/አሳዳጊ ወይም ቤተሰብ ወይም ደባል በማጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት ውንጀላ የሚጠረጠር ሲሆን) በማንኛውም የተጠረጠረ የማጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት ክስ ለተነካ/ች ተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች ወድያውኑ ማሳወቂያ ፕላን ያዳብራሉ። በነዚህ ሁኔታዎች፣ CPS፣ APS (ለዳካማ አዋቂዎች)፣ ወይም የMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል/Special Victims Investigations Division ለወላጆች/አሳዳጊዎች ለማስታወቅ ሀላፊነት አለባቸው።

2. ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ግንኙነት ለማቃለል ከተፈለገ MCPS ምስጢራዊ የትርጉም አገለግሎቶች ያቀርባል።

3. ተፈፀመ ስለተባለ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ለወላጆች/አሳዳጊዎች ማን ማስታወቅ እንዳለበት ውሳኔዎች እና ማስታወቂያ መቸ እንደሚከናወን የሚወሰነው በርእሰመምህሩ/ሯ ከMCPD ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ እና ከካውንቲ MDT ተባባሪ ወኪል ድርጅቶች ጋር በመመካከር ነው።

4. (a) የMontgomery County የጤናና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምርያ የጠባቂነት ሀላፊነት ወይም ተማሪውን አንስቶ ወደ መጠለያ እንዲወስድ ስልጣን ካለው፤ ወይም (b) በተጠረጠረው መጎሳቆል ወይም ቸልታ ምክንያት ህክምና አስፈልጎ ካልሆነ በስተቀር ያለወላጅ ፈቃድ አንድም ተማሪ ለጥያቄ ወይም ለህክምና ምርመራ ከት/ቤት ቅጥርት ግቢ ውጭ መወሰድ የለበትም/ባትም።

5. አንድ ተማሪ ሲ/ስትወገድ፣ ረሰማምህሩ/ሯ የመወገዱን ማስታወቂያ ለወላጆች/አሳዳጊዎች ወድያው መደረጉን ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች። በጋራ ስምምነት፣ እንደዚህ አይነቱ ማስታወቂያ ለCPS፣ ለAPS፣ ወይም ለMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል ሊመራ ይችላል።

E. **ሌሎች የት/ቤት ማህበረሰብን ማስታወቅ**

1. ርእሰመምህሩ/ሯ ከMCPD ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ፣ የMCPS የልጅ ማጎሳቆል አስተባባሪ ቡድን አባሎች፣ የመገናኛ ፅ/ቤትና OSSIን ጨምሮ፣ እና ከካውንቲ MDT ወኪል ድርጅቶች ጋር በመተባበር ሌሎች የት/ቤት ማህበረሰብ አባሎች ማወቅ እንዳለባቸው፣ ይህን ለመፈጸምም የጊዜ ገደብ ጨምሮ፣ መወሰንና ፕላን ማዘጋጀት።

   a. ማንኛውም ምርመራ በእንጥልጥል ላይ እያለ እና ሰው ከመታሰሩ ወይም ክስ ከመመስረቱ በፊት፣ ለት/ቤት ህብረተሰብ ማስታወቁ:- (1) ተጠቂ ለተባለው ተቀዳሚ ጥቅም እንደሆነ፤ ወይም (2) በመካሄድ ላይ በሚገኝ ምርመራ ጣልቃ ይገባ እንደሆነ ለመወሰን ርእሰመምህሩ/ሯ ከMCPD ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ፣ የMCPS የልጅ ማጎሳቆል አስተባባሪ ቡድን አባሎች፣ የመገናኛ ፅ/ቤትን ጨምሮ፣ እና ከካውንቲ MDT ወኪል ድርጅቶች ጋር የተባበራል።

   b. የካውንቲ MDT ተባባሪ ወኪል ድርጅቶች በMCPS ንብረት ወይም በMCPS ስፖንሰረድ በሆነ እንቅስቃሴ ወይም የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛን የሚያካትት የልጅ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ተፈፅሟል የተባለን የሚያካትት የመታሰር አዝማሚያ ወይም የወንጀል ክስ ምስረታ የሚያውቁት ነገር ካለ MCPSን በቅድሚያ ያስታውቁታል። MCPS የካውንቲ MDT ተባባሪ ወኪል ድርጅቶች የማሰር ተግባርን በተቻለ መጠን ከት/ቤት ቅጥር ገቢዎች ርቀውና ከትምህርት ሰአቶች ውጭ እንዲያደርጉ ያበረታታል።

   c. በMCPS ንብረት ተፈፀመ ስለተባለው የመጎሳቆልና የቸልተኝነት ክውነት ምክንያት ሰው እንደታሰረ ወይም ክስ እንደተመሰረተ MCPS ሲያውቅ፣ ርእሰመምህሩ/ሯ፣ ህብረተሰቡ በሚገባ እንዲያውቅ፣ ከMCPD ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ፣ የMCPS የልጅ ማጎሳቆል አስተባባሪ ቡድን አባሎች፣ የመገናኛ ፅ/ቤትና OSSIን ጨምሮ፣ እና ከካውንቲ MDT ወኪል ድርጅቶች ጋር ይተባበራል።

2. MCPS የማህበርሰብ ማስታወቂያ ትግባሬን ለመፈፀም የሚጥረው በነዚህ ሁኔታዎች ነው:- (a) የተባለው ማጎሳቆል ወይም ቸልተኛነት የነካቸው ተማሪዎችና ቤተሰቦች ምስጢራዊነትንና እምነትን ይጠብቃል፤ (b) በት/ቤቱ ማህበረሰብ የሚገኙ ሁሉንም ተማሪዎች ደህንነት በሚያረጋግጥ መንገድ ክሶቹን በሚገባ እንደያዛቸው ለማህበረሰብ ለማረጋገጥ መረጃ ያቀርባል፤ እና (c) የሜሪላንድ የህዝባዊ መረጃዎች ህግ አግባብ ያላቸውን መርሆች መከተልን ጨምሮ፣ አጥቂ ለተባለው ህጋዊ መብቶች በመጠበቅ ረገድ ተግቶ ይጠነቀቃል።

3. የማንኛውም የማህበረሰብ ማሳወቂያ ደብዳቤ፣ ኢሜይል፣ ወይም ኤለክትሮኒክ የቃል መልእክት ቅጅዎች ከMCPD ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ተጠሪ፣ የMCPS የልጅ ማጎሳቆል አስተባባሪ ቡድን አባሎች ጋር ይጋራሉ።

4. በካውንቲው MDT ተሳታፊ የሆኑ ወኪል ድርጅቶች ከማህበረሰብ አባሎች የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኛነት ምርመርራዎቻቸውን በሚመለከት ለሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች መልስ በመስጠት የMCPS ሰራተኞችን ለመደገፍ ተስማምተዋል።

## IV. <u>ምስጢራዊነት፣ ከተጠያቂነት ነፃ መሆን፣ ከበቀል መጠበቅ</u>

A. በሜሪላድ ህግ፣ ማንም ሰው በቀና መንፈስ በማጎሳቆል ወይም በቸልተኛነት ዘገባ የሚያከናውን ወይም በዘገባ የሚሳተፍ ወይም በምርመምራ ወይም በውጤቱ የህጋዊ ዳኝነት ሂደት የሚሳተፍ የማጎሳቆል ወይም ቸለተኛነት ዘገባ በማድረግ ወይም በምርመራ ወይም በህጋዊ ሂደት በመሳተፍ ሊደርስ ከሚችል የፍትህብሄር ባለእዳነት ወይም የወንጀለኛ ቅጣት ነፃ ነው።

B. በሜሪላድ ህግ፣ ማንም የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ሆነ ብሎ በማጎሳቆልና ቸልተኛነት ዘገባ ማጨናገፍ ወይም ጣልቃ መግባት አይችልም።

C. የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች በቀና መንፈስ ቀርበው ስለ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ ሲያቀርቡ እና/ወይም የማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ምርመራ ውስጥ ሲሳተፉ፣ MCPS በነዚያ

ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችል ከማስፈራራት፣ ወከባ፣ ወይም በቀል ሊጠብቃቸው ይጥራል።

D. ተማሪዎች የማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ተጠቂዎች ወይም ምስክሮች ሲሆኑ ወይም በቀና መንፈስ ቀርበው ስለ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ ሲያቀርቡ እና/ወይም የማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ምርመራ ውስጥ ሲሳተፉ፣ MCPS በነዚያ ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችል ከማስፈራራት፣ ወከባ፣ ወይም በቀል ሊጠብቃቸው ይጥራል።

E. ሁሉም የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች በህግ ምንጩን እንዲገልፁ ካልተጠየቁ በስተቀር የዘገባ አቅራቢውን ማንነት መከታ ሆነው እንዲጥብቁ ይፈለግባቸዋል።

## V. ሆን ብሎ/እያወቁ የማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ አለማቅረብ ወይ ዘገባ ሲደረግ ጣልቃ መግባት የሚያስከትሏቸው ውጤቶች

A. ማንኛውም የMCPS ሰራተኛ፤ በሙያ ችሎታው/ዋ ለMCPS የሚሰራ፣ የልጅ መጎሳቆል የሚጠረጥር/የምትጠረጥርና ሆን ብሎ/ላ ዘገባ ያላቀረበ/ች፣ ወይም ሆን ብሎ/ላ ዘገባ እንዳይቀርብ የሚታገል/የምትታገል ወይም ጣልቃ የሚገባ/የምትገባ፣ እስከ እገዳ ወይም ስንብት የሚደርስ የዲሲፕሊን እርምጃ ይጠብቀዋል/ይጠብቃታል።

B. ማንኛውም የMCPS ስራ ተቋራጭ፤ በአገልግሎት ችሎታው/ዋ ለMCPS የሚሰራ፣ የልጅ መጎሳቆል የሚጠረጥር/የምትጠረጥርና ሆን ብሎ/ላ ዘገባ ያላቀረበ/ች፣ ወይም ሆን ብሎ/ላ ዘገባ እንዳይቀርብ የሚታገል/የምትታገል ወይም ጣልቃ የሚገባ/የምትገባ፣ እስከ የአገልግሎቶች መቋረጥ የሚደርስ የዲሲፕሊን እርምጃ ይጠብቀዋል/ይጠብቃታል።

C. ማንኛውም የMCPS በጎ-ፈቃደኛ፤ በበጎ-ፈቃድ ችሎታው/ዋ ለMCPS የሚሰራ፣ የልጅ መጎሳቆል የሚጠረጥር/የምትጠረጥርና ሆን ብሎ/ላ ዘገባ ያላቀረበ/ች፣ ወይም ሆን ብሎ/ላ ዘገባ እንዳይቀርብ የሚታገል/የምትታገል ወይም ጣልቃ የሚገባ/የምትገባ፣ እስከ የበጎ-ፈቃድ ልዩ መብቶች መቋረጥ የሚደርስ የዲሲፕሊን እርምጃ ይጠብቀዋል/ይጠብቃታል።

D. በተጨማሪ፣ በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ ወይም በሌላ ፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት ሰጪ ወጪ የተደረገ ማንኛውም የምስክር ወረቀት በሜሪላንድ ህግ፣ የሜሪላንድ ደንብ (COMAR) 13A.12.05.02 ጨምሮ፣ ሊታገድ ወይም ሊነሳ ይችላል።

## IV. ከማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ጋር የተያያዙ አመፆች የሚያስከትሏቸው ውጤቶች

**A.** MCPS አንድ የMCPS ሰራተኛ በማጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት ውስጥ ተግኝቶ/ታ ከሆነ ወይም የMCPSን መመርያዎች፣ ደንቦች፣ ወይም የMCPSን የሰራተኛ ስነምግባር ደንብ/Employee Code of Conduct ጨምሮ አመራር መጣሱ(ሷ)ን ካረጋገጠ፣ ግለሰቡ/ቧ እስከ መታገድ ወይም ስንብት ጨምሮ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበ(ባ)ታል።

**B.** MCPS አንድ የMCPS ስራ ተቋራጭ ወይም በጎ-ፈቃደኛ በማጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት ውስጥ ተግኝቶ/ታ ከሆነ ወይም የMCPSን መመርያዎች፣ ደንቦች፣ ወይም አመራር መጣሱ(ሷ)ን ካረጋገጠ፣ ግለሰቡ/ቧ እስከ የአገልግሎቶች ወይም የበጎ-ፈቃደኛ ልዩ መብቶች መቋረጥን ጨምሮ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበ(ባ)ታል።

**C.** በተጨማሪ፣ በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ ወይም በሌላ ፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት ሰጪ ወጪ የተደረገ ማንኛውም የምስክር ወረቀት በሜሪላንድ ህግ፣ COMAR 13A.12.05.02 ጨምሮ፣ ሊታገድ ወይም ሊነሳ ይችላል።

## VII. የሙያ እድገት

A. MCPS፣ የካውንቲ MDT ተባባሪ ወኪል ድርጅቶችን ጨምሮ ከሀገራዊና ከአካባቢ ወኪል ድርጅቶች የባለሙያ ድጋፍ ጋር፣ የMCPS ሰራተኞች ይህን ደንብ በመተግበር ላይ ተገቢ ሞያዊ እድገት/ስልጠና ያቀርባል።

1. ከተማሪዎች ጋር መስራት ከመጀመራቸው በፊት፣ ሁሉም አዳዲስ የMCPS ሰራተኞች የልጅ ወይም የደካማ አዋቂ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት መለየት፣ ዘገባ ማቅረብ፣ እና መከላከል አስገዳጅ ስልጠና ይቀበላሉ። OHRD ሁሉም የMCPS ሰራተኞች ይህን አዲስ የቅጥር ስልጠና መፈፀማቸውን የሚያረጋግጡ መዛግብት ይይዛል።

2. በያንዳንዱ የትምህርት አመት መጀመርያ ላይ፣ ሁሉም ነባር የMCPS ሰራተኞች የልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት መለየትና ዘገባ ዝግጅት ወቅታዊ እውቀትና ግንዛቤ መኖሩን ለማረጋገጥ አስገዳጅ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ግምገማ የሚያካትት ስልጠና ይፈፅማሉ። ስልጠናዎች በድርጅቱ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ሰራተኞች ፍላጎቶች እንደሚስማሙ ሆነው በተለይ ተስተካክለው በግምባር ወይም በመስመር ላይ ትምህርት በማካተት ይዘጋጃሉ ። እንደ አግባቡ፣ ስልጠናው ለተጠርጣሪ አመፀኞች ህጋዊ ሂደትንም ይመለከታል። ሁሉም የMCPS ሰራተኞች አስገዳጅ የመድህን የምስክር ወረቀት በየአመቱ መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ OHRD መዛግብት ይይዛል።

B. ከብሄራዊና ከአካባቢ የባለሙያዎች ድጋፍ ታክሎበት፣ የካውንቲ MDT ተባባሪ ወኪል ድርጅቶችን ጨምሮ፣ MCPS፣ ስለ ልጆችና ደካማ አዋቂዎች ማጎሳቆልና ቸልተኛነት መለየት፣ ዘገባ ማዘጋጀት፣ እና መከላከል እንዲሁም እነዚህን ጉዳዮች በሚመለከት የMCPS መመርያዎችና ደንቦች ለMCPS በጎ-ፈቃደኞችና ስራ ተቋራጮች፣ እንዲሁም ወላጆችና በሰፊው የMCPS ማህበረሰብ ለሚገኙ ሌሎች፣ እንደግባቡ፣ ዎርክሾፖች፣ መረጃዎች፣ እና መስመር ላይ የስልጠና ሞዲውሎች ያቀርባል።

C. በተጨማሪ፣ የMCPS ሰራተኞች ቀጥተኛ ቁጥጥር በሌሉባቸው ሁኔታዎች ተማሪዎች ጋ መድረስና መገናኘት የሚችሉ የMCPS በጎ-ፈቃደኞች እና ስራ ተቋራጮች፣ ለMCPS ሰራተኞች ከሚሰጠው የሙያ ስልጠና ጋር ተመጣጣኝ ይዘት ያለው ማጎስቆልንና ቸልተኛነትን መለየት፣ ዘገባ ማቅረብ፣ እና መከላከልን የሚመለከት እንደአግባቡ ስልጠና የተቀበሉ እና/ወይም መረጃያዊ ቁሳቁሶች የገመገሙ መሆናቸውን ማስመስከር ይፈለግባቸዋል። የምስክር ወረቀት ፎርሞቹን ቅጂዎች MCPS ይይዛል።